# <u>ለአምባ ገነኖች እምቢኝ! የማለት ድፍረት!!</u>
# The Courage to Say NO! To Dictators!!




The famous photograph in which August Landmesser refused the Nazi salute. It was in 1936 during the celebrations for the launch of a ship, the *'Horst Wessel'*.

**ኦጉስት ላንድመሰር የተባለ ጀርመናዊ ነበር በናዚው ሂትለር ዘመን በ1936 እኤአ በአንድ የመርከብ ምረቃ በዓል ላይ: በበዓሉ አብረው የተገኙት በሙሉ፤ የጀርመን ናዚ ሠላምታ ለሂትለር ሲያቀርቡ፤ እሱ ብቻ ነበር የናዚዎችን ሰላምታ ለሂትለር ላለማቅረብ እንቢ በማለት እጆቹን አጣምሮ በፎቶው ላይ የሚታየው::**
**(በነገራችን ላይ ፎቶውን አሳድጋችሁ ማየት ትችላላችሁ)**




**ግፍን ላለማየትና ላለመስማት ዓይናቸውን ጨፍነውና፤ ጆሯቸውን በሸንፍላቸው ውስጥ ቀብረው በየሚያንኮራፉና፤ እያዩ በማያዩ፤ ለሕሊናቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ባደሩ ብዙ ነብሶች መሃከል፤ የሕይወት ጥሪያቸውን የሚያዳምጡ ጥቂት ነብሶች አሉ፤ ከነዚህ መሃከል አንዱ ጀርመናዊው ኦጉስት ላንድመሰር ሲሆን፤ በአገራችን በኢትዮጵያም በተለያዩ ዘመናት፤ በዘመነ መሳፍንት፤ እንደ ልጅ ካሳ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ፤ በፋሽስት ጣልያን ወረራ ዘመን፤ እንደ አብረሃምና አስገዶም ደቦጭ፤ ዘርአይ ደረስ፤ አብዲሳ አጋ፤ በአጼ ኃ/ሥላሴ ዘመን እንደ በላይ ዘለቀ፤ ግርማሜና መንግስቱ ንዋይ፤ ጥላሁን ግዛው፤ በደርግ ዘመን የአየር ሃይል የጦር መኮንኖች፤ እንደ አቤ ጉበኛውና በዓሉ ግርማ....ወዘተ. የመሳሰሉ ለሃቅ፤ ለፍትሕ፤ ለነፃነት፤ ለአገራቸው ክብርና ለወገናቸው ፍቅር ሲሉ ከሕዝባቸው ጎን በመቆም አምባ ገነኖችን በቆራጥነት በመፋለም እንቢ! በማለት፤ የመጨረሻውን የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል ::**

EthioLion.Com

የትግል ስልቱ ይለያይ እንጂ ዛሬም አበበ ገላው በአሜሪካን አገር በተደረገው የ8ቱ በእንዱስትሪ የበለጸጉ አገሮች ስብሰባ ላይ፤ አገራችን ኢትዮጵያን በሚገባት ክብርና ሞገስ ሳይሆን፤ በድህነት የልመና አቁማዳቸውን ይዘው፤ ኢትዮጵያን ለማዋረድ በለማኝነት ተርታ ተመድበው በስብሰባው ላይ የተገኙት አቶ መለስ ዜናዊን ላገራቸው ክብር፤ ለዲሞክራሲና ለፍትህ እንዲሁም ለሕዝባቸው ብልጽግና ያልቆሙ፤ እንዳውም ገበሬውን እያፈናቀሉ የኢትዮጵያን ለም መሬት ለድንበር ዘለል ከበርቴዎች እየቸበቸቡ፤ ሕዝባቸውን በረሃብ አለንጋ የሚያስገርፉ፤ የማሰብ፤ የመናገርና የመጻፍ መብት በመግፈፍ ዜጎችን በግፍ የሚያስሩ፤ እንዲሰደዱ የሚያደርጉ፤ ጨካኝ አንባ ገነን መሆናቸውን ከመላው ዓለም የመጡ ልኡካን እንዲያውቁት አድርጓል ::

የሚገርመው አቶ መለስ ዜናዊ ባለ ሁለት አሃዝ እድገት አስመዝግበናል እያሉ በፓርላማ ተብያቸው እየፎለሉ ሳለ፤ እንደገና የልመና ስልቻቸውን ይዘው ወደ ምድረ አሜሪካ የምግብ ዋስትና ስምምነት (Alliance for Food Security) በተባለ ስብሰባ ላይ ለመገኘት መምጣታቸው፤ የተባለው ዕድገት ከጉንጭ ማልፋት ያልዘለለ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ከማሳየቱም በላይ ሕዝባችን የሰቃይ ኑሮ በመኖር ላይ ያለ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው ::

አቶ መለስ አያቶቻችንና የቅድም አያቶቻችን የህይወት መስዋዕትነውት የከፈሉበትን የአገራችንን መሬት ለሕንዶች፤ ለአረብ አገራትና ለቻይና የሚቸበችቡት አልበቃ ብሏቸው ለምዕራባውያን በዘባቹ ኮርፖሬሽኖች እንደ **ሞሳንቶስ** ለመሳሰሉ፤ የተለያዩ አዝርዕትን አጥፍቶ፤ አንድ ወጥ በሆነ የድቀላ ዘር፤ የተደቀለ ትወልድ አፍርቶ ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ ለማድረግና የሕዝብዝችንን ጉልበት ለማሰበዝበዝ፤ የምግብ ዋስትና ስምምነት (Alliance for Food Security) በሚል ስብሰባ ለመሸጥ ሊያስማሙን ብቅ አሉ::

የአቶ መለስ አስተዳደር በመንግሥታዊ ሌቦች የታጀበና የተሞሸረ ብልሹ ለመሆኑ እራሳቸውም ያመኑበት ጉዳይ ሲሆን፤ የሚገርመው መንግሥታዊ ሌቦቻቸውን በብብታቸው ውስጥ ታቅፈው እያሞላቀቁና የኢትዮጵያን ሕዝብ በርሃብ አለንጋ እያስገረፉ ስለ ልማት ማውራቱ ምን ያህል ተአማኒነት እንደሚያሳጣቸው መገመቱን ዛሬም አልተረዱም፤ ወይም በአቶ መለስ ዜናዊ ዘመን « ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ » የሚለው መርህ በአዋጅ ጸድቋል ::

ያም ሆነ ይህ አበበ ገላው በአገራችን ኢትዮጵያ ፍትሕ፤ ነፃነት፤ አንድነትና እኩልነት ከዳቦ በላይ አስፈላጊ መሆናቸውን ለስብሰባው ተካፋዮች፤ ከማስረዳቱም በላይ፤ ኢትዮጵያን የመሰለች የነፃነት ቀንዲልና ለም አገር ይዞ፤ በረሃብተኞች ስብሰባ ላይ ለማኝ ሆኖ መገኘት ምን ያህል አሳፋሪ መሆኑን ለአቶ መለስ ዜናዊና ለተከታዮቻቸው ትልቅ ትምህርት ሰቷል :: (የመማር ፍላጎቱ ካለ !!)

ለፍትሕ የበላይነት፤ ለነፃነት፤ ለአገሩና ለወገኖቹ ክብር በመቆሙ፤ የሁላችንም ባለውለታ ነውና አበበ ገላው ሊመሰገን ይገባል ::

*ክረምቱ ሊያበቃ ወራቱ ቀረበ፤*
*እሸቱ ሊያሸት ነው አበባው አበበ::*

ብዬ ቋጠርኩልህ::

(ወንድምህ አሥራደው ከፈረንሳይ)

ግንብቦት 12 2004ዓ.ም. (May 20/2012)